ቀኀለ
# እስከመቼ
ሕዳር
፳፻፫ ዓ. ም. ቅፅ ፮ ቁጥር ፭
November 2011 Vol. VI No. 5

# የኔሰው ገብሬ

## የኔሰው ገብሬ

### የኔሰው ገብሬ

የኮንቻ ሰማይ
ደፈረሰ፤
በየኔነህ ደም
ተወረሰ፤
የኮንቻ አየር
ፎገራ፤
በየኔሰው
ደም ተጣራ።

የኔሰው
ገብሬ፤
ባንተ
እኖራለሁ
ከብሬ።

ጣፍ ሆኖ
በርቶ፤
መንገዳችንን
አጥርቶ፤
የትንታግ ነዶው
እየመራ፤
እየጎመራ
እየጠራ፤
ያገሬን ሰማይ
እያበራ፤
መጣ የኔሰው
እየጎደራ።

መምር ነህ
ብለውኝ፤
ሕፃናትን መሪ
አዳኝ፤
ወጣትነህ
ብለውኝ፤
ተወዳጅና
ተመስጋኝ፤
ሌት ተቀን
ታታሪ፤
ለዕምነቱ
ተጠሪ፤
የሕዝቡን ብሶት
ተናጋሪ።

ሠልፍህ
ካቡነ ጴጥሮስ
ከሽብሬና
ከቴዎድሮስ፤
ሀውልት ነህ
የምታበራ
ከሩቅ ታይታ
ምታስፈራ።

ምርኩዝ ነህ
ባለሙያ
ፅናትህ ኃያል
ያገር መኩሪያ።
ብሶትህ
ጮኾ ባገሬ፤
ሲቃህ
ተሰምቶ በመንደሬ፤
ወገኔ ከፍቷል
ጎሊናውን፤
እጁን ዘርግቷል
ያጣውን።

ልቤ
በሳት ጋለ፤
አንጀቴ ሥሩ
ተኮማተረ፤
ቃለ ገባሁ
ደግሜ ዛሬ፤
ልሸከምህ
አምርሬ።

ሀገር
ጧፍ ያብራለት
ዳር እስከ ዳር
ያንድድለት፤
ለተንቀለቀለው
ለቆመለት
ለየኔሰው
ላማረበት።

ከርቻ አበራች አሉኝ
ተንቀልቅላ ደምቃ፤
የኔሰው ሆኖላት
የሕዝቡ ጠበቃ።

eske.meche@yahoo.com
ሀገሬ ተመቼ፤ ዋና አዘጋጅ